# የመሀል ከተማ ገቢር እቅድ ማጠቃለያ

ሲያትልን መሀል ከተማ እስኪ አብረን እንቀይር።

ወረርሽኙ እንዴት እንደምንኖር እና እንደምንሰራ ለውጦታል፣ ይህ ማለትም አዲስ መሀል ከተማን ለመገመት እድል ሰጠን። ለከተማው እምብርት አዲስ የወደፊት ሁኔታን ለመገንባት – እንደ አንድ ሲያትል – አብረን ልንሰራ እንችላለን። ደህንነቱ የተጠበቀ፣ እንግዳ ተቀባይ እና ልዩ የሆነ የማህበራዊ መሰብሰቢያ ቦታ የመሀል ከተማ መፍጠር እንችላለን። ትንንሽ/ ወጣቶች ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች ተደራሽነት ያለው እና በዋጋ ተመጣጣኝ የሆነ መሃል ከተማ። ለአካባቢ የአየር ንብረት ጥበቃ ተስማሚ፣ አረንጓዴ እና የሚያምር መሃል ከተማ። ትናንሽ፣ የተለያዩ ንግዶች የሚበለፅጉባት እና የሚያድጉባት መሃል ከተማ።

ህይወት እና ቀለም የሞላባት መሃል ከተማ። እርስዎን የሆነች መሃል ከተማ።

ከንቲባ ብሩስ ሃረል (Bruce Harrell) የመሃል ከተማ ገቢር ፕላን በመባል የሚታወቀውን መሃል ከተማ ሲያትልን እንደገና ለማደስ የቀረበውን የሲያትል ከተማን እቅድ አውጥተዋል። እቅዱ ነዋሪዎች፣ ሰራተኞች፣ እና ጎብኚዎች ጊዜ ለማሳለፍ ወደሚፈልጉበት ቦታ መሃል ከተማን ለማረጋጋት እና ለመቀየር ደፋር ግቦችን እና እርምጃዎችን ያስቀምጣል። እቅዱ የሲያትልን በዘር እና በማህበራዊ ፍትህ እሴቶች ተጠብቀው ለመኖር ይጥራል። እንዲሁም መለካት የሚችሉ ውጤቶችን፣ ግልጽ የጊዜ ሰሌዳዎችን እና ተጠያቂነትን ደግሞ ያካትታል።

ከተማው የሚከተሉትን ሰባት ግቦች እና ስልታዊ ዘዴዎችን ለማሳካት ይሰራል:

1. መሃል ከተማን **ደህንነቱ የተጠበቀ** እና መልካም አቀባበል ያለው ማድረግ።
2. መሃል ከተማን ብዙ ሰዎች በተመጣጣኝ ዋጋ መኖር ወደሚችሉበት ወደ ህይወት ሰጭ **ሰፈር** መቀየር።
3. ልዩ የሆነ የ**ችርቻሮ** ልምድ የመሀል ከተማ መፍጠር።
4. መሃል ከተማ ሰዎች **እንዲሠሩባት** የሚፈልጉበት እና የወደፊቱን ኢኮኖሚያችንን የሚያንፀባርቅ ቦታ ማድረግ።
5. **የጥበብ፣ የባህል፣ የስፖርት፣ እና የመዝናኛ** መሀል ከተማ ሲያትልን ያክብሩ።
6. መሃል ከተማ ለሲያትል ተወላጆች እና ለጎብኚዎች አመቱን ሙሉ **ከፍ ያለ መዳረሻ** ማድረግ።
7. ጤናማ፣ ጠንካራ እና **አረንጓዴ** መሃል ከተማ መፍጠር።

ዕቅዱ በሦስት የተለያዩ የጊዜ ሰሌዳዎች/ ቅደም ተከተሎች እርምጃዎችን ይዘረዝራል:

- **ደፋር እርምጃዎች አሁን** – ወዲያውኑ የሚጀምሩ ተነሳሽነቶች።
- **የቅርብ ጊዜ ተነሳሽነቶች** – በሚቀጥሉት ሶስት አመታት ውስጥ የሚፈጸሙ ጥረቶች።
- የ**ጠፈር መርፌ (Space Needle) አስተሳሰብ** – ለወደፊት መሃል ከተማ ሲያትል ባለ ራዕይ ሀሳቦች።

የመሃል ከተማ ገቢር እቅድ የመሀል ከተማን የወደፊት ሁኔታ ለእርስዎ ግልጽ አድርጎ ያወጣል። **መሃል ከተማ እርስዎ ነዎት።**

## ስለዚህ እቅድ እና ስለወደፊት የራዕይ ሀሳቦች ምን ያስባሉ? ከእርስዎ መስማት እንፈልጋለን!

እባኮትን ይህንን **የመሀል ከተማ ገቢር እቅድ ግብረ መልስ ቅጽ** በመጠቀም አስተያየትዎን ያካፍሉ።



ስለ የሲያትል ከተማ መሃል ከተማ ገቢር እቅድ ለበለጠ መረጃ እና ግብረ መልስዎን ለማጋራት፣ downtownisyou.comን ይጎብኙ።

ቅጹ በተለያዩ በዙ ቋንቋዎች ተተርጉሟል። የእቅዱን የትርጉም ድጋፍ ለመስጠት እና የግብረ መልስ ቅጹን እንዲያስገቡ ለመርዳት የሁለት ቋንቋ ተናጋሪ ሰራተኞች ዝግጁ ናቸው። **የቋንቋ እርዳታ የሚፈልጉ ከሆነ፣ እባክዎን (206) 684-8090 ይደውሉ።**

የእርስዎ ምላሽ የመሀል ከተማ ገቢር እቅድ በጋራ ማጠናከር እና እንደገና ማጥራታችንን እንድንቀጥል ይረዳናል።

*የሲያትል ከተማ፣ እያንዳንዱን ሰው በፕሮግራሞቹ እና በእንቅስቃሴዎቹ እንዲሳተፍ ያበረታታል። ለተጨማሪ ጥያቄዎች፣ ለትርጓሜ ወይም በቃል ለማስተርጐም፣ ለቴክኒካዊ ድጋፍ፣ ለአካል ጉዳተኞች መስተንግዶዎች፣ በተለዋጭ ቅርጸት ላሉ ቁሳቁሶች/ መረጃዎች ወይም የተደራሽነት መረጃ ለማግኘት እባክዎ የኢኮኖሚ ልማት ቢሮን በ (206) 684-8090 ወይም oed@seattle.gov ያግኙ።*



ስለ የሲያትል ከተማ መሃል ከተማ ገቢር እቅድ ለበለጠ መረጃ እና ግብረ መልስዎን ለማጋራት፣ downtownisyou.comን ይጎብኙ።